የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የዋሽንግተን ዲሲ እና አካባቢው
ሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Archdiocese of Washington DC
and its surroundings.

ታህሳስ 29 ቀን 2003 ዓ.ም

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ**

**አሜን**

በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ልደት፤ ከዓመተ ፍዳ ወደ ዓመተ ምሕረት የተሸጋገራችሁ ፤ ለአባታችን ለአዳም የተሰጠው ተስፋ የተፈጸመላችሁ ፤ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኛችሁ ፤ አባቶቼና እናቶቼ ወድሞቼና እኅቶቼ ፤ በአጠቃላይ በአለንበት አገር በሰሜን አሜሪካና በሀገራችን በኢትዮጵያ በመላው ዓለም ለምትገኙ ወገኖቼ በሙሉ ከሰማየ ሰማያት የወረደው ከቅድስተ ቅዱሳን ከድንግል ማርያም የተወለደው ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና ይግባውና ፤ እንኳን ለበዓለ ልደቱ በሰላምና በረድኤት ጠብቆ አደርሳችሁ ፤ በማለት የእንኳን አደረሳችሁ መንፈሳዊ መልእክቴን በዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት ስም ሳቀርብ በታላቅ አክብሮት ነው።

**"ወበጽሑ ውስተ ኢየሩሳሌም እንዘ ይብሉ አይቴ ሀሎ ዘተወልደ ንጉሠ አይሁድ"**

የተወለደው የአይሁድ ንጉስ ወዴት አለ እያሉ ኢየሩሳሌም ደረሱ፡፡ ማቴ ፪ ፡ ፪

የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በሞት ጥላ ስር ለወደቀው ለሰው ልጅ ድኅነት ትንቢት የተነገረለት ፤ ዘመን የተቆጠረለት ፤ ቃል ኪዳን የተገባለት ነው። እንደ እንግዳ ደራሽ አይደለም፡፡ ትንቢቱ ተፈጽሞ ለማየት የሰው ልጅ ወደቀደመ ክብሩ ተመልሶ ፈጣሪውን ከመላእክት ጋር እያመሰገነ በደስታ እንዲኖር በመመኘት ብዙ ነቢያት ጻድቃን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የጮሁበትም ነው። በመሆኑም ርቆ የነበረው ዘመን ቀርቦ ትንቢቱ ተፈጽሞ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በቤተልሔም ትንቢት ከተነገረላት ለእናትነት ከተመረጠችው ከድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ ከተሾሩው ባለቤቶች ከአይሁድ እና ከንጉሱ ከሄሮድስ ይልቅ ቀድመው የሰሙትና የተረዱት በኢየሩሳሌምም የተገኙት ከሩቅ ምሥራቅ በኮከብ ተመርተው እጅ መንሻውን ይዘው የአይሁድ ንጉስ ወዴት አለ ልንሰግድለት መጥተናልና በማለት የክርስቶስን መወለድ ለንጉሱ ያረዱት ሰባሰገል ነበሩ። ይህም ማለት የክርስቶስ ልደት በአስተሳሰባቸው ደካማ ለነበሩት ለንጉሥ ሄሮድስና ለመሰሎቹ መርዶ ሲሆን በተስፋ ሲጠባበቁ ለነበሩት ለእረኞቹና ለመሰሎቻቸው ደግሞ ብሥራት ነበረ። ህሊናው በፈላጭ ቆራጭነት የደነደነውና ምድራዊነቱን ረስቶ ራሱን በአልሞት ባየነት ያታለለው ፤ ንጉሥ

ሄሮድስ የክርስቶስን መወለድ ሲሰማ **“ደነገጠ ኢየሩሳሌምም ሁሉ ከእርሱ ጋር”** ሰብአ ሰገል የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? የሚል ጥያቄ ሲአቀርቡ ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት ድኅረ ዓለም ከቅድስተ ቅዱሳን ከድንግል ማርያም ያለአባት  የተወለደው  ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ  ንጉሠ ሰማያት ወምድር መሆኑን አውቀውና አምነው ሊሰግዱለት ፤ እጅ መንሻ ወርቅና እጣን ከርቤም ሊአቀርቡለት ነበር። ምኞታቸውም ተፈጽሞላቸው ወርቁን ለመንግሥቱ እጣኑን ለክህነቱ ከርቤውን ለሞቱ በቤተልሔም ተገኝተው ከስግደትና ከምስጋና ጋር ለአምላካቸውና ለንጉሣቸው አቀረቡ። በተቃራኒው ለሰማያዊ ክብር ያልታደለው ሄሮድስ ሰብአ ሰገልን **“ሂዱ ስለሕጻኑ በጥንቃቄ መርምሩ ባገኛችሁትም ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ አላቸው”** የሄሮድስ ፍለጋና ምርምር ሊሰግድለት ወይም እጅ መንሻ ሊአቀርብለት አልነበረም። የጌታ መልአክ ለዮሴፍ በህልም እንደነገረው **“ሄሮድስ ሕጻኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ”** ሲል  ከንቱ ምኞቱንና ሀሳቡን ድብቅ ዓላማውን ማንነቱን የእግዚአብሔር መልአክ ቢገልጥበትም ሰብአ ሰገልም እንደተሳለቁበት ቢረዳም ከአሰበው ክፉ ሀሳብ አልተመለሰም። **“በቤተልሔምና በአውራጃዋ የነበሩትን ሁለት አመት የሆናቸውን ከዚያም የሚያንሱትን ሕጻናት ሁሉ አስገደለ”**። ይሁን እንጂ ምድራዊ  ደካማ ነበርና ሞት ገዛው ሞኞቱም ከንቱ ሆነ። በእሱ ምክንያት የተሰደዱት  ከስደት ተመለሱ እሱ ግን የሁለት ዓለም ስደተኛ  ሆነ። የክፉ ሰው መጨረሻው ይህው ነውና።

የታደሉት እረኞች ደግሞ ከመላእክት ጋር **“ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ”** የመወለዱን ብሥራት ከመላእክት ሰሙ ፤ በአንድነትም  ዘመሩ እግዚአብሔር የገለጠላቸውንም ለማየት እስከ ቤተልሔም ገሰገሱ። በእርግጥም እንደተነገራቸው “ማርያምንና ዮሴፍን ሕጻኑንም በግርግም ተኝቶ አገኙ”።

ወገኖቼ  ቅዱስ መጽሐፍ ከዚህ በላይ በተገለጸው መልአኩ እንዳስተማረን **“የአይሁድ ንጉሥ ወዴት አለ”** የሚለዉን ጥያቄ ለጽድቅም ለኰነኔም ለበጎም ለክፉም ተጠቅመውበታል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ምዕ ፭ ፡ ፬ **“የሚያሳፍር ነገርም የስንፍና ንግግርም ወይም ዋዛ የማይገቡ ናቸውና አይሁኑ ፤ ይልቁን ምስጋና እንጂ”** ይላል። ሄሮድስና መሰሎቹ  ከሚያሳፍር ነገር ከዋዛ ፈዛዛ ከስንፍና ለመራቅ ጨርሶ ባለመሞከራቸው አላዋቂነታቸውንና ስንፍናቸውን  አጉልተው  አሳይተዋል። በእርግጥም  የስንፍና ንግግር ያሳፍራል ፤ ዋዘኛነትም ፈጽሞ የማይገባ ነው። አሳፋሪ ነገርና ስንፍና ባይጠናወታቸው አስተሳሰባቸው ባይደክም  በቤተልሔም የተወለደው ከዘመናት በፊት የነበረ ዘመናትን አሳልፎ የሚኖር  የሚታየውንና  የማይታየውን  የፈጠረ  የሁሉ ገዢ የሁሉ ባለቤት መሆኑን አምነው እንደ ሰብአ ሰገል በሰገዱ በገበሩ ፤ እንደረኞቹ ከመላእክቱ ጋር ባመሰገኑ ነበር። ነገር ግን ከምስጋና ይልቅ የማይረባ ነገር ማረካቸው። በመሆኑም በአሳፋሪ ንግግራቸው በስንፍና ጠባያቸው በደካማ አስተሳሰባቸው  በምሳሌነት  ሲጠቀሱ ይኖራሉ።

በሌላ መልኩ ከስንፍና ተላቀዉ ከአሳፋሪ ንግግር አንደበታቸውን ከልከለው እንደ ሰብአ ሰገል እና እንደእረኞቹ ከአምላካቸው ጋር የሚገናኙበትን መንገድ ለሚሹ ሁሉ **"በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘለዓለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል"** በማለት በሮሜ ፪ ፡ ፯ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ፤ ሰብአ ሰገልና እረኞቹ በበጎ ሥራ በመጽናት በአደረጉት ጉዞ በገበሩት አሥራትና በአቀረቡት ምስጋና በምሳሌነት ተጠቅሰዋል ፤ የዘለዓለምንም ሕይወት ወርሰዋል። ምንጊዜም እግዚአብሔርን የሚፈልጉና ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖሩ ከበጎ ሥራ አይለዩም አስተሳሰባቸውም ሰማያዊ ነው። አንደበታቸውም ሰላማዊ ነው። ክፉ ዘር አይዘሩም። ከመከራ ሊታደጋቸው የመጣላቸውን አምላካቸውን ይቅርና ጠላታቸውን አያሳድዱም፡፡

ስለዚህ ወገኖቼ የሁሉንም ታሪክ ከዚህ በላይ ሰምተነዋል በሰማነውና በአወቅነውም ታሪክ እንደየዘርፉ ተደስተናል አንድም አዝነናል። ስለሆነም እንደአበው ብሂል ታሪክ መስተዋት ነውና ራሳችንን በሰብአ ሰገልና በእረኞች ፤ በንጉሡ ሄሮድስና በመሰሎቹ መስተዋትነት እንድናይ ግድ ይለናል። እንደሚታወቀው መስተዋት የሆነውን ነገር ለማሳየት አይፈራም። ይሉኝታም የለዉም። ማንነታችንን አንብቦ ሰብአ ሰገልን ወይም በብሥራተ መልአክ የተበሰሩትን ፤ በልዩ ብርሃን የተከበቡትን ፤ ከሰማያውያን ጋር የዘመሩትን ፤ በደስታ ተመልተው እየዘለሉ ወደ ቤተልሔም የገሰገሱትን አድርጎ ራሳችንን ያሳየናል። ከዚህ ካለፈም ሸፍጥና ማታለል ማሳደድና ግድያ ከፊቱ የሚነበበውን ሄሮድስን አድርጎ ማንነታችንን ማጋለጡ የማይካድ ሐቅ ነው።

በልደተ ክርስቶስ ከጨለማ ወደብርሃን ፤ ከባርነት ወደልጅነት ፤ የተመለሳችሁ ወገኖቼ በሙሉ ፤ ሰብአ ሰገል በኮከብ ተመርተው ኢየሩሳሌም ከደርሱ በኋላ ኮከቡ ቢሰወራቸው "የተወለደው የአይሁድ ንጉስ ወዴት አለ?" የሚል ጥያቄ ማቅረባቸው ይታወሳል። በሄሮድስ ንግግርም ሳይታለሉ የተሰወራቸውን ኮከብ አይተው ቤተልሔም መድረሳቸውና አምሀ ማቅረባቸው አይዘነጋም። ዛሬም በተለያዩ ምክንያቶች ከአገራችን ወጥተን በዓለም ዙሪያ የምንኖር ሁሉ ፤ ቅደመ ዓለም የነበረው ድኅረ ዓለም ከቅድስተ ቅዱሳን ከድንግል ማርያም በቤተልሔም የተወለደው በንጹሕ ደሙ የመሠረታት ጥንታዊቷና አማናዊቷ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወዴት አለች ብለን ልንጠይቅ ይገባል፡፡ ዓላማቸውን በሳቱ ሰዎች ተታለን ያለን መስሎን ከምስጋናው ግምጃ ቤት እንዳንወጣ ልንጠነቅቅ ያስፈልጋል። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የራቁትንም የራሳቸው ባልሆነ ትምህርትና ሥርዓት ተይዘው የሚገኙትንም ማንነታቸውን በማወቅ ስህተታቸውን እንዲያውቁ ልንነግራቸው ፤ ካፈርን

አይመልሰን ያሉትንም ልናውቅባቸው ፤ ከስህተታቸው የተመለሱትን ልናቀርባቸው ፤ ቤተ ክርስቲያናችንን እንደ ዐይን ብሌን ልንጠብቃት እምነት ግድ ይለናል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ **"ነግር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል**" ይላል፡፡ ሮሜ ፪ ፡ ፲ ክርስቲያን መሆንና ክርስቲያን መባል የሚታወቅበት ምልክቱም ይህ ነው። በጎ የሚሠራ ክብር አለው፡፡ በጎ የሚሠራ ሰላም አለው፡፡ በጎ የሚሠራ ይመሰገናል። በጎ ሥራን ዘመን አይሽረውም። በመሆኑም ለበጎ ሥራ እንነሳሳ ስለቅድስት ቤተክርስቲያናችን አንድነትና ሰላም በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት የተለያየን ተገናኝተን የተራራቅን ተቀራርበን ታሪክ ጠባቂዎች እንሁን። በአንድነት ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ በማለት እንድንዘምር፡፡ የየበኩላችንን ድርሻ ተግተን የቅዱሳን አባቶቻችንን አምላክ በጸሎት እንጠይቀው፡፡ ሌላውን ነገር ሁሉ ትተን ለሰላሙ ተልእኮ አቅማችን በሚፈቅደው መንፈሳዊ ሥራ ሁሉ እንተባበር።

በዚሁ አጋጣሚ በግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እና ምእመናት በደረሰባቸው ሰው ሠራሽ አደጋ በሀገረ ስብከቱ ስም ኃዘናችንን እንገልጻለን ለኃዘንተኞችም እግዚአብሔር መጽናናትን እንዲሰጥልን እንለምናለን። ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩትም እረፍተ ነፍስ እዲሰጥልን እንማጸናለን።

**በክርስቶስ ክርስቲያን ወገኖቼ ፤**

በአጠቃላይ **"አንድነታችንን አንተው"** ነገር ሳይሆን መብአ ይዘን ለክርክር እና ለውዝግብ ሳይሆን ለምስጋና ክርስቶስ ወደ ተወለደባት ቤተልሔማዊት ቤተክርስቲያናችን እንገስግስ በውስጧም ተገኝተን ከመላእክቱ ጋር እንቀድስ እናስቀድስ፡፡ በድጋሜ እንዳለንበት አገር ዘመን አቆጣጠር እንኳን ለአዲሱ አመት እና ለብርሃነ ልደቱ አደረሳችሁ፡፡

እግዚአብሔር አምላካችን ለሀገራችን ለኢትዮጵያና ለመላው ዓለም ሰላምን ይስጥ

ምድረ አሜሪካንንም በረድኤት ይጠብቅልን

አባ አብርሃም

የዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት

ሊቀ ጳጳስ